legal aiddc

## የቤት ውስጥ ጥቃት ከደረሰብዎ እና ለባለሙያ ሪፖርት ያደረጉ ከሆነ፣ በዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ የክራይ ውልዎን እንዴት ማቋረጥ እንደሚችሉ

ዲሲ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ እና የቤት ውስጥ ጥቃት ከደረሰብዎ፣ የክራይ ውልዎን ሳይጠናቀቅ የማቋረጥ መብት አሎት። **የክራይ ውልዎን ሳይጠናቀቅ ለማቋረጥ ስለፈለጉ የቤት አከራይዎ ገንዘብ ሊያስከፍልዎ ወይም ተቀማጭ ገንዘብዎን ለመቁረጥ አይፈቀድለትም ።**

ሶስት ቅደም ተከተሎችን በመከተል የክራይ ውልዎን ሳይጠናቀቅ ያቋርጡ፡-

**ቅደም ተከተል 1፡- ለባለሙያ የደረሰብዎትን የቤት ውስጥ ጥቃት ሪፖርት ያድርጉ። ሪፖርት እንዳደረጉ የሚያሳይ የተፈረመ ሰነድ ያሳዩዋቸው።**

*እዚህ ላይ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ፡- (1) ለጤና ባለሙያ፣ ልክ እንደ ሐኪም እና ነርስ፣ (2) የሰለጠነ የቤት ውስጥ ጥቃት አማካሪ፣ (3) ለፖሊስ መኮንን፣ **ወይም** (4) ከ DC የቤቶች ባለስልጣን የደህንነት መኮንን።*

**ቅደም ተከተል 2፡- ሁለተኛው ገጽ ላይ ዓባሪ የተደረገው ደብዳቤ ይሙሉ።**
*ይሄ ደብዳቤ የቤት ክራይ ውሎን እያቋረጡ እንደሆነ ለአከራይዎ ያሳውቃል። ደስተኛ ስላልሆኑ ብቻ የእርስዎን ተቀማጭ ገንዘብ መያዝ እንደማይችሉ ያሳውቃቸዋል። ለእርስዎ (ተከራይ) እና ለእርስዎ አከራይ አንዳንድ መሰረታዊ መረጃ ማከል ያስፈልጎታል።*

**ቅደም ተከተል 3፡- ለአከራዮ ደብዳቤ ይላኩ <u>እና</u> የቤት ውስጥ ጥቃት ሪፖርት የሚያሳይ ሰነድ ያሳዩዋቸው።**

*ኢሜይል ሊያደርጉት፣ በደብዳቤ ሊልኩት ወይም በአካል ሊሰጧቸው ይችላሉ። ማስታወሻ፡- ቅጂውን ይያዙ። የቤት ውስጥ ጥቃት ሪፖርት ያደረጉበትን ኦርጅናል መረጃ **እንዳይሰጡ**።*

**ቅደም ተከተል 4፡- አስተማማኝ የሆነ አድራሻ አንዴ ካገኙ በኋላ፣ የተቀማጭ ገንዘብዎን የሚልኩበት አስተማማኝ አድራሻ ለአከራይዎ ይንገሯቸው።**

**ይሄ ላይ ምን ያህል መስራት አለብኝ?** የዲሲ ሕግ የክራይ ውልዎን ጊዜው ሳይጠናቀቅ እንደሚያቋርጡ ለአከራይዎ ለመንገር ክስተቱ ሪፖርት ከተደረገበት ቀን ጀምሮ **90 ቀናት** (ወደ 3 ወር ) ገደማ ይሰጦታል።

*የቤት አከራይዎ ገንዘብ ሊያስከፍልዎ ወይም ተቀማጭ ገንዘብዎን ሊያስቀር የሚሞክር ከሆነ፣ ሕግ እንደጣሱ ሊቆጠር ይችላል። የቤት አከራይዎ ምን እንደሚያደርጉ ጥያቄ ያለዎት ከሆነ፣ በ (202)-628-1161 ላይ ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ [www.legalaiddc.org/online-intake](http://www.legalaiddc.org/online-intake)።*

*የጥበቃ ትዕዛዝ የሌለዎት ከሆነ እና ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ፣ ዲሲ ሴፍ (DC SAFE)ን በ (844) 443-5732 ላይ ደውለው ያግኙ ወይም የዲሲ የቤት ውስጥ ጥቃት ፍርድ ቤት ክፍል ቢሮን (D.C. Court Domestic Violence Division Clerk’s office) (202) 879-0157 ላይ ደውለው ያግኙ።*

***እገዛ ይፈልጋሉ?** (202) 628-1161 ላይ ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ [www.legalaiddc.org/online-intake/](http://www.legalaiddc.org/online-intake/)።*

______________________________________
የእርስዎ ስም

______________________________________
የእርስዎ የደብዳቤ አድራሻ

______________________________________
ቀን

______________________________________
የቤት አከራዩ ስም ወይም የቤት አቅራቢው ስም

______________________________________
የእርስዎ ቤት አከራይ የደብዳቤ አድራሻ

ጉዳዩ፡ <u>በዲሲ ደንበ ሕግ § 42-3505.07 መሰረት የቤት ክራይ ውል የማቋረጥ ማስታወቂያ</u>

ውድ የቤት አቅራቢ፡-

እኔ፣ ____________________________፣ ይሄንን ደብዳቤ የምጽፈው በእኔ የተከራየሁበት ቤት ቁጥር ______________________ ላይ ያለኝን የክራይ ውል የማቋረጥ ፍላጎት እንዳለኝ በመደበኛ ሁኔታ ለማሳወቅ ነው። በዲሲ ሕገ ደንብ § 42-3505.07 መሰረት፣ ያለምንም የቅጣት ክፍያ ማሳወቂያ በደረሰዎ አስራ አራት (14) ቀናት ውስጥ የእኔን የክራይ ውል ማቋረጥ ይጠበቅቦታል ምክንያቱም፡-

1. በዲሲ ሕገ ደንብ ቁጥር § 16-1001(8) መሰረት የቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂ ነኝ፣ እና
2. ብቁ በሆነ ሶስተኛ ወገን የተፈረመ ሰነድ አለኝ(ቅጂው ተያይዟል)።

በዲሲ ሕገ ደንብ ቁጥር § 42-3505.07 መሰረት፣ ፣ ከሁለቱ የትኛው ቀድም አንዱ ቢመጣም፣ ከዛሬ ጀምሮ የሚቆጠር ለ 14 ቀናት ያሀል ውጪ የቤት ክራይ ሊያስከፍሉኝ አይችሉም ወይም የቤት ክራዩን ለሌላ ሰው ማከራየት አይችሉም። የክራይ ውሉን ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት ስላቋረጥኩኝ ተቀማጭ ገንዘቤን መቁረጥ **አይችሉም**። ዲሲ ሕገ ደንብ § 42-3505.07 *ይመልከቱ።* ተቀማጭ ገንዘቡን ለእኔ መልሰው እንዲልኩልኝ የሚልኩበት አድራሻ አሳውቆታለሁኝ።

ማንኛውም ዓይነት ጥያቄዎች ያለዎት ከሆነ፣ እባክዎን በዚህ አድራሻ ያግኙኝ ____________________________። እናመሰግናለን።
ስልክ ወይም የኢሜይል አድራሻ

ከአክብሮት ጋር፣

ፊርማ (የተከራይ ፊርማ)

**በተጨማሪም በደብዳቤ ውስጥ፡-** በብቁ ሶስተኛ ወገን የተፈረመ ሰነድ ቅጂ